# የሕዝብ ትግል በውሸትና በአሉባልታ አይጨናገፍም

ከዚህ በፊት በአንዲት ትንሽ ጽሑፍ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ቅንጅትና የቅንጅት ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ትግል ከባድ ፈተና ላይ ናቸው። ፈተናውም ከባድ የሆነበት ምክንያት ቅንጅትና የቅንጅትን ትግል ለማዳከምና ለማፍረስ የሚሯሯጡት በቅንጅት ውስጥ ያሉና ወደ ቅንጅት ከመምጣታቸው በፊት የወያኔን ሥርዓት ሲያጠናክሩና ሲመክሩ የነበሩ ጥቅመኞችና መልዕክተኞች በመሆናቸው ነው።

ለምሳሌ ያህል የማዳከሙንና የመከፋፈሉን ሶስት ቀንደኛ መልዕክተኞች እንመልከት፤
አንደኛ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ቀደም ብሎ አሜሪካን አገር ተማሪ በነበረበት ወቅት ለአቶ መለስ ዜናዊና ለአቶ ኢሳያስ አፈወርቂ የሕዝብ ስብሰባ መድረክ እያዘጋጀ ኢትዮጵያን የመከፋፈሉንና የማዳከሙን ትግል ሲደግፍ ቆይቷል። በዚሁ ጊዜ ከፕሮፌሰር እንድርያስ እሸቴና አቶ ክፍሌ ወዳጆ ጋር በመሆን "እምቢልታ" የሚል መጽሔት በማዘጋጀት የኢትዮጵያን ህልውና "ቦዲ ፖለቲክ" ሲያዳክሙና ለጠላት ሲያጋልጡ ቆይተዋል። ፕሮፌሰር እንድርያስ እሸቴና አቶ ክፍሌ ወዳጆ ለወያኔ ሥርዓት ምን ሚና እንደተጫወቱ ማብራራቱ አስፈላጊ አይደለም። ቀጥሎም ወያኔ ባባረራቸው ምርጥ ኢትዮጵያዊ ፕሮፌሰሮች አንደኛው ተተኪ በመሆን ተቀጥሮ ለአመታት አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ አስተምሯል። በዚሁ የማስተማር ጊዜው የአቶ መለስ ዜናዊ የኢኮኖሚክ አማካሪና የቴኒስ ጫወታ ጓደኛቸው መሆኑ ይነገርለታል። ከዚህም ሌላ ከምላሳቸው መርዝ ከሚንረፈው ቀንደኛ ወያኔ አቶ በረከት ስምዖን ጋር ልዩ ወዳጅነት እንዳለው ብዛት ተነግሯል። ወዳጅነታቸው አሁንም የጠበቀ መሆኑ ይነገራል። የንግድም ሥራ በከፍተኛ ደረጃ አካሂዷል፤ አሁንም ጭምር።

እነዚህን ጥቂት ነጥቦች ደምረን በአንድነት ብናያቸው የዶክተር ብርሃኑ ቅርበትና ትስስር፣ ታማኝነትና ድጋፍ ለወያኔ እንጂ ለቅንጅት እንዳልሆነ መገመት ከባድ አይደለም። ይህንን መሳይ የወያኔ ትስስርና ቅርበት ይዞ ነው ወደ ቅንጅት ምስረታ የመጣው። እርሱና ፕሮፌሰር መሥፍን ወልደማርያም ወደ ቅንጅት ምሥረታ ይዘውት የመጡት ቀስተ ደመና ፓርቲ የተቋቋመው ቅንጅት ከመቋቋሙ ከአስር ቀናት በፊት ነበር። ለዚህም ፓርቲ ምዝገባ የሚያስፈልገውን የአንድ ሺህ አምስት መቶ (1500) አባላት ተሯሩጠው ያስፈረሙለት የመኢአድ አባላት ናቸው። የአስር ቀናት ሕይወት ያለው፣ አንዳችም ሕዝብ የማደራጀት ሥራ ያልሠራ፣ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያለውን ራዕይና ፕላን ያላቀረበ፣ ታሪክና ክንውን የሌለው ድርጅት ይዘው ነው የግዙፍ ድርጅት አቻ ሆነው የቅንጅት ታላቅ መድረክ ላይ የወጡት። ከመድረኩ ላይ ወጥተው በአባል ብዛት ስሌት አንድ ወንበር እንኳን የማይገባቸው ሰዎች 12 ወንበር ተሰጣቸው። ይህንን ልገሳ እነርሱ እንደሞኝነት ቆጠሩት። ክቡር አቶ ኃይሉ ሻውል ተሞኝተው ሳይሆን ዓላማቸው ወያኔን ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ በሰላማዊ ትግል ማውረድ ስለነበረ፣ ቀስተደመና ስንት ወንበር አገኘ፣ አደፓ መድሕን ስንት ወንበር አገኘ አልበረም። ዶክተር ብርሃኑ ግን ገና ከጠዋቱ የተንኮልና የመከፋፈል ስራውን ይሠራ ነበር።

ሁለተኛ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ወያኔ ሥልጣን በኃይል ከመያዙ በፊት እንግሊዝ አገር ይኖር የነበረና የአቶ መለስ ዜናዊ ወዳጅ ሲሆን፣ ወያኔም በብቸኝነት ኢትዮጵያን እንዲቆጣጠር ሙሉ ድጋፍ የሰጠ ሰው ነው። ከዚያም ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ የአዲስ አበባ ምክትል ከንቲባ ሆኖ ወያኔን በታማኝነት አገልግሏል። ከዚህም ሌላ ወያኔ ዳኞች ሲሾም የሱን ግምትና ሚዛን እንደሚጠይቅ እራሱ በጽሑፉ አስቀምጦታል። ምናልባትም ወይዘሮ ብርቱካን ሚዴቅሳንም ለዳኝነት ያጫት እሱ ሳይሆን አይቀርም።

በተጨማሪም ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት እንዲጠፉ ሟት ማታ የሚሮጠው የአቶ ተፈራ ዋልዋ አማች ነው:: የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ እህት የአቶ ተፈራ ዋልዋ ባለቤት ናት:: እነዚህን ጥቂት ነጥቦች ደምረን በአንድነት ብናያቸው አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ቅርበቱና ታማኝነቱ ለወያኔ እንጂ ለቅንጅትና ለኢትዮጵያ ሕዝብ አይደለም:: ስለ ኢትዮጵያና ስለአማራው ሕዝብ የጻፈውን ማየት በቂ ነው:: አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ከአውሮፓ (ከለንደን) ጠርቶ ቅንጅት ውስጥ የተከለው ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ነው:: አምጥቶ የተከለውም ቅንጅትን እንዲያዳክምና እንዲከፋፍል መሆኑ አሁን ግልጽ ሆኗል:: ስለአመጣጡና ዶክተር ብርሃኑ ስለሰጠውም ሹመት ሁለቱ አልተስማሙም:: እኛ በቅጡ አላዳመጥነውም እንጂ እሱ አኮ የኔ መሪ ዶክተር ብርሃኑ ነው እያለ ማውራት ከጀመረ ቆይቷል:: እንዲያውም በአንድ የቅንጅት ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች ጉባኤ ላይ "ቅንጅት እኔን ፈልጎ መጣ እንጂ እኔ ቅንጅትን ፈልጌ አልመጣሁም" ብሏል:: እውነቱ ግን ዶክተር ብርሃኑ ፈልጎ ቅንጅት ውስጥ አመጣብን እንጂ ቅንጅት አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ፈልጎ አላመጣም:: አሁንም ቅንጅት አሱን አይፈልግም:: ፈልጎትም አያውቅም:: ለሁለት ዓመት የቅንጅት ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶችን ለመከፋፈልና ለማዳከም ያላደረገው ጥረትና ያልሸረበው ተንኮል የለም:: ለምሳሌም ያህል "ቅንጅት ኢንተርናሽናል ሊደርሺፕ" "ኮሌክቲቭ ሊደርሽፕ" "ዲሞክራሲያዊ አወቃቀር" እያለ ያልፈጠረው ማወናበድ የለም:: እያንዳንዱ ተንኮል ጠለቅ አድርጎ ሲያዩት የማጭበርበሪያ ባዶ ቀፎ ሆኖ እናገኘዋለን::

ሶስተኛ አቶ ብርሃነ መዋ የዶክተር ብርሃኑ ነጋ ወዳጅና የንግድ ሽሪክ ነው:: በወያኔ ሥርዓት የነጋዴዎች ምክር ቤት ፕሬዚዳንት የነበረና የራሱ የንግድ ድርጅቶች ያለው ሰው ነው:: አሁንም ንግዱና ንብረቱ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል:: የአቶ ክፍሉ ታደሰ መጽሐፍ "ግንቦት 7" እንደሚለው አቶ ብርሃነ መዋ አገርና ንብረት ጥሎ የተሰደደው አስራ አባት ሺህ የሚያህል ታክስ ክፍያ አጭበርብረሃል ተብሎ ለ15 ቀናት ከታሰረ በኋላ የተባለውን ገንዘብ ከመክፈል ይልቅ ወደ አሜሪካ ስደትን መርጦ ወደዚህ መጣ:: ጉዳዩ ከኬንያ በፍጥነት ተጠናቆ አሜሪካ ገባ:: በነገራችን ላይ አቶ ብርሃነ መዋ በብዙ ሚሊዮን የሚገመት ንብረት በኢትዮጵያ እንዳለው ይነገራል:: ታዲያ ይህን ያህል ንብረት ያካበተ ሰው አስራ ሰባት ሺህ ብር መክፈል አቅቶት ነው የሚሰደደው? ይሄ ለሰሚው ግራ ነው:: ምንድነው ወደ አሜሪካ ግስገሳው ዋና ምክንያት? እንዴትስ እቅንጅት ውስጥ ገባ? እሱንም መልምሎ ቅንጅት ውስጥ እንዲገባ ያደረገው ዶክተር ብርሃኑ ነው:: ሁሉም እንደሚያውቀው በወያኔ ኢትዮጵያ ማንም ሰው እንኳን ትልቅ ድርጅት ቀርቶ ኬክ ቤት እንኳን ለመክፈት ወያኔ የማይፈልገው ሰው ከሆነ ምንም ዓይነት እድል የለውም:: አቶ ብርሃነ መዋ ወያኔ አቅፎ ተንከባክቦ ሐብታም ያደረገው ታማኝ ደጋፊ ነው:: ላለፉት ሁለት ዓመታት የቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶችን ሲያምስና ሲያበጣብጥ የነበረ የዶክተር ብርሃኑ ቀንደኛ መልዕክተኛ ነው:: ወያኔን ወያኔ አትበሉ እያለ የሚቆጣ ሰው ነው:: እነዚህን ጥቂት ነጥቦች አንድጋ ደምሮ ላያቸው ሰው አቶ ብርሀነ መዋ ቅርበቱ፣ ታማኝነቱና አገልግሎቱ ለወያኔና ለዶክተር ብርሃኑ ነጋ ነው? ወይስ ለቅንጅትና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ? መልሱ ግልጽ ነው::

የእነዚህ ሶስት ሰዎች በቅንጅት ውስጥ ያላቸውን ዕድሜ፣ ትግልና አስተዋጽኦ ብንመለከት እያንዳንዳቸው ስለራሳቸው ከሚሉት የፈጠራ ሥራና አስተዋጽኦ በስተቀር ይህ ነው የሚባል ምስክር የሚናገረው አንዳችም ነገር የለም:: ነገር ግን ዶክተር ብርሃኑ በጻፈው መጽሐፍ ውስጥ ያለአንዳች ሐፍረት እሱ ብቻውን ቅንጅትን እንደፈጠረና ለዚያ ትልቅ ድል እንዳበቃው ተናግሯል:: "እግዚአ መሐረነ ክርስቶስ" ከማለት ሌላ ምን ይባላል? ጥረቱ ግን ማንን

ለማታለልና ለማሳመን ይሆን ? ሕዝብ የሚያውቀውንና ያየውን ሀቅ ለውጦ ማቅረብ እመጥፎ ግምት ውስጥ ከማስገባት ሌላ የሚሰጠው ጥቅም የለም:: ሙከራው ግን እራሱን ለመሪነት ቦታ ሲያመቻችና እወቁኝ ለማለት ነው:: የአራዳ ልጅ ሥራ ይሏል ይሄ ነው፡

እንደሚነገረው ከሆነ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ከንቲባነቱን ሥራ ትቶ ወደ ለንደን የመጣው ባጀት ወጥቶለት በአውሮፓ ምንም ዓይነት የወያኔ ተቃዋሚ ቡድን እንዳይፈጠር ለማድረግና ከተፈጠረም በዘዴ ለመበታተን የተላከ የወያኔ ባለሚል ነው:: እውነትም በአውሮፓ ያሉትን የቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶች እንዴት አድርጎ እንደከፋፈላቸውና የእርሱና የዶክተር ብርሃኑ ደጋፊዎች እንዳደረጋቸው ስንመለከት ለጥፋት ሥራ በአውሮፓ እንደተቀመጠ ግልጽ ሆኖ ይታያል፡ የሚያደርገውንም ወዲህ ወዲያ ጉዞና ቆይታ ስንመለከት በበጀት እንደሚንቀሳቀስ ጠ ርቶ ይታያል:: አለበለዚያማ ቋሚ ሥራ ይዞ እራሱን የማያስተዳድር ሰው እንዴት ሊሆንለት ይችላል?

በተመሳሳይ ሁኔታ አቶ ብርሃነ መዋ ወደ አሜሪካ እንደተላከ የሚናገሩ አሉ፡ ይህም ግለሰብ በተመሳሳይ ሁኔታ ወዲያ ወዲህ የሚንቀሳቀስ፣ ነገር ግን ሰርቶ እራሱን የሚያስተዳድር ግለሰብ አይደለም:: በጀቱ ምን ያህል እንደሆን ባይታወቅም በአንድ የቅንጅት ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች ጉባኤ ላይ ቅንጅት ኢንተርናሽናል ሊደርሽፕ ተጠሪነቱ ለድጋፍ ድርጅት ካልሆነ የጠየቀው ልዩ በጀት አይሰጥም ቢባል "እናንተ ባትሰጡን እኛ ከምናገኝበት እናመጣለን" በማለት በቁጣ መናገሩ ሲያስፈልገው እጁን የሚያስገባበት የገንዘብ ሳጥን እንዳለ መስክሯል:: ያም የገንዘብ ሳጥን የተዘጋጀውና የተመደበው ቅንጅትን ለመከፋፈልና ለማዳከም መሆኑ ግልጽ ነው::
ይህንን ሁሉ አጠያያቂ አመጣጣቸውንና አጠፌ ተልእኳቸውን ለመደበቅ የሚጠቀሙበት ዘዴ ሌሎች የቅንጅት አጀንዳ አራማጆች ላይ አሳፋሪ ውሸትና አሉባልታ ማራገብና ማናፈስ ነው:: ውሸቱንና አሉባልታውን የሚያራግቡበትና የሚያናፍሱበት ብዙ ድኅረ ገጾች፣ሬዲዮ ጣቢያዎችና ፓልቶክ ክፍሎች በሰፊው ዘርግተዋል:: ኢትዮጵያን ሪቪው፣ ከረንት አፌርስ፣ ኢትዮ ፎረም፣ አቡጊዳ፣ አዲስ ፎይስ ሬዲዮ፣ ኢትዮሚዲያ ወዘተ... እነዚህንም መድረኮች የሚያካሂዱ ብዙ ካድሬዎች አሏቸው:: ካድሬዎቹ ደግሞ ለውሸት፣ ለስድብ፣ ለአሉባልታ፣ ሥራ በጥንቃቄ የተመረጡ ስለሆኑ በሉ የተባሉትን ከማለት፣ አድርጉ የተባሉትን ከማድረግ ወደኋላ አይሉም:: አመዛዛኝና አሳቢ አእምሮ እንዳለው ሰው ነገሮችን አውጥተው አውርደው ውሸቱን ከእውነት ለይተው ትክክለኛውና እውነተኛውን መንገድ ይዘው አይደለም የሚሄዱት:: የአገርና የሕዝብ አጀንዳ በእነሱ ዘንድ ትርጉምና ቦታ የለውም:: የአገርና የሕዝብ አጀንዳ የሚያራምዱ የተለያዩ የስም ማጉደፊያ ቅጽል ይሰጣቸዋል:: አጸያፊ ስድብ ይሰደባሉ:: የፈጠራ ወንጀል ይለጠፍባቸዋል:: በመታመማቸው ይፌዝባቸዋል:: ብስለትና አዋቂነታቸው ይፌዝበታል፡ ቆራጥነታቸው፣ ጀግንነታቸው፣ እውነተኛነታቸው፣ ለአገርና ለሕዝብ ያላቸው ፍቅርና ታማኝነት፣ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያላቸው ብሩሕ ራዕይና ተስፋ ግትርነት፣ አክራሪነት፣ ዲክቴተርነት እየተባለ ይቀለድበታል፣ ይፌዝበታል::

በክቡር አቶ ኃይሉ ሻውል የሚመራው እውነተኛው የቅንጅት ትግል እዚህ ወራዳና አሳፋሪ ተግባር ላይ በማተኮር ከዋናው አጀንዳ እንዲርቅና የዕለት ተዕለት ትኩረቱን ለእነርሱ አሉባልታና ስድብ መልስና ማብራሪያ በመስጠት ጊዜውንና ጉልበቱን እንዲያባክን ይፈልጋሉ:: በየቀኑም አዲስ ውሸት አዲስ አሉባልታ ይፈጥራሉ:: በመሀሉ ወያኔ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እንደልቡ ይቦርቃል::

በክቡር አቶ ኃይሉ ሻውል የሚመራው ቅንጅት ከእንግዲህ ወዲያ ጊዜውንና ትኩረቱን መስጠት ያለበት ወደዚያ ብዙ ኢትዮጵያኖች ሕይወታቸውን ለሰዉለት፣ ብዙ ኢትዮጵያኖች ለተሰቃዩለት፣ አካለ ጎደሎ ለሆኑለት፣ ለተሰደዱለት፣ አሁንም ለሚሰቃዩለት ማለትም ሕዝብ ለመረጠው መንግሥት፣ ለሕግ የበላይነት፣ ለነጻ ፍርድ ቤት፣ ለነጻ የሀገር መከላከያ፣ ለነጻ ፕሬስ፣ ለነጻ የምርጫ ሕግና ቦርድ፣ ለነጻና ግልጽ የሕዝብ ምርጫ ትግል መሆን ይገባዋል። ይህ እስካልሆነ ድረስ የነሱ ወያኔን ማጠናከርና የኢትዮጵያን ሕዝብ በዘላለማዊ ሥቃይና መከራ ውስጥ ማቆየት አጀንዳ ግቡን ይመታል። ነገር ግን እውነቱ፣ ሀቁ ተደጋግሞ መነገር አለበት ይህም እየተደረገ ነው። ነገር ግን ለአሉባልታና ለውሸት ጊዜ ማጥፋት እነሱ ወጥመድ ውስጥ ዘሎ መግባት ነው።

እረ ለነገሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ የማያውቀው እውነት አለ? የኢትዮጵያ ሕዝብ እውነቱን ጠንቅቆ ያውቃል። ማን እንደሚታገልለትና መስዋዕትነት እንደሚከፍልለት ጠንቅቆ ያውቃል። አሁን መስማት የሚፈልገው አይዞህ በአታላዮችና በወያኔ ምንደኞች ውሸትና አሉባልታ አትደናገጥ፤ የማታውቃቸውና የማያውቁህ የአራዳ ጮሌዎች በውሸትና በአሉባልታ ግራ ሊያጋቡህ እየተሯሯጡ ነው። አትሞኝላቸው ማለት አስፈላጊ ጉዳይ ነው።

በተለይም የበግ ቆዳ የለበሱ ተኩላዎች መሆናቸው ይነገረው። እነሱ የሚፈልጉት በስሙ ነግደው ሀብትና ዝና ማትረፍ መሆኑ ይገለጽለት። ጉዞ ማለዳ ነውና ይህ ጉዞ አሁኑኑ ይጀመር። ከተጀመረም እሰዬው! እነዚህ አቃቂ ድረስ እንኳን ሄደው ሕዝብ ያላደራጁ የአራዳ ጮሌዎች ስለኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎትና ችግር መናገር አይችሉም። ይህ የኢትዮጵያን ሕዝብ አለማወቅና አለማደራጀት ጉድለት ተሰምቷቸው ይመስላል ወይዘሮ ብርቱካን  አንዴ ሱሉልታ፣ አንዴ ወላይታ እየሄደች ፎቶግራፍ የምትነሳው። ውጣ ውረዱ የተካሄደው ከምርጫ 1997 ዓ.ም ሶስት አራት ዓመታት በፊት ነበር። የዚያን ከገጠር ወደ ከተማ የማደራጀት እውነተኛ መሐንዲስ ክቡር አቶ ኃይሉ ሻውልን አሁን ኮፒ ማድረግ ከንቱ ውዳሴ ነው። ያልዘሩት አዝመራ አይታጨድምና ይህ ብልጣ ብልጥነት ይቁም። እሳቸው ያንን ያደረጉት በፎቶግራፍ ለመታየት ብለው አልነበረም። የእውነተኛ ትግል መሰረቱ ሕዝብን ማደራጀትና ማስተማር መሆኑን ጠንቅቀው ስላወቁ ነው።

የሆነው ሆኖ ይህ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ከወያኔ ጥቃት፣ ግፍና በደል ማዳን የክቡር አቶ ኃይሉ ሻውልና የአመራራቸው ብቻ ግዴታ አይደለም። የሁሉም ኢትዮጵያዊ ሃላፊነትና ግዴታ ነው። ጥቂቶች ሲታገሉ፣ መስዋዕትነት ሲከፍሉ ሌሎቻችን እዳር ቆመን ታዛቢዎች ልንሆን አንችልም። የአገርና የሕዝብ ግዴታ አለብን። ኢትዮጵያዊነት ግዴታም ጥቅምም አለው። ጥቅሙን ብቻ እየፈለግን ግዴታውን ልንሸሽ አንችልም። ይህ ለሁላችንም ግልጽ መሆን አለበት። አንዳንዶቻችን ግን የግል ጥቅማችንና ድሎት እስከተጠበቀ ድረስ የአገርና የሕዝብ ጉዳይ ምናችንም አይደለም። አገር ጠፋ ኖረ ጉዳያችን አይደለም። እንደነዚህ ያሉ ሰዎች ልንከተላቸው ወይንም ምሳሌ ልናደርጋቸው አይገባም። ስለሆነም በወያኔና በውጭ ኃይል የተገዙ የአገርና የሕዝብ ጠላቶች ዲሞክራሲና የሕግ የበላይነት በኢትዮጵያችን እንዳይሰፍን በውሸትና በአሉባልታ ሕዝብ ግራ ሲያጋቡ እዳር ቆሞ ማየት ወይንም በዩልኝታ እነሱን ማዳመጥ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያ ሕዝብ መጉዳታችን መሆኑን ተገንዝበን ውሸትና አሉባልታ አንሰማም አንቀበልም ማለት ይጠበቅብናል፡ እዚህ ላይ ኤሌኖር ሮዝቬልት (Eleanor Roosvelt) ያሉትን መጥቀስ አግባብ ይመስላል፤ " Staying aloof is not a solution. It is a cowardly evasion." በተመሳሳይ ሁኔታ ኤድመንድ በርክ (Edmund Burke) ያሉትም

ወቅታዊነት አለው፤ " The only thing necessary for the triumph of evil is for good people to do nothing." ስለዚህ የቅንጅትን ትግል ከግቡ ለማድረስ፣ ማለትም የኢትዮጵያን ሕዝብ ውሳኔ ለማስከበር እያንዳንዳችን የምንችለውን አስተዋጽኦ ማድረግ ግዴታ አለብን:: ድል ሲገኝ ድሉ የሁላችንም ነው:: ኢትዮጵያ ውስጥ ዲሞክራሲና የሕግ የበላይነት ሲሰፍን ጥቅሙ የሁላችንም ነው:: የዘር ፖለቲካ ከኢትዮጵያ ሲወገድ ጥቅሙ የሁላችንም ነው:: ድህነት፣ ረሃብ፣ ድርንቁርና፣ በሽታ ከኢትዮጵያ ሲወገዱ ጥቅሙ የሁላችንም ነው:: ኢትዮጵያ ስትከበርና ስትፈራ ክብሩ የሁላችንም ነው:: ታዲያ ጥቅሙ የጋራችን ከሆነ ትግሉን የጥቂቶች ብቻ አድርገን የምናየው ለምንድነው? እነኚህ ጥቂቶች ምን የተለያ ግዴታ ኖሮባቸው ነው ለብቻቸው የሚታገሉት? ምንም የተለየ ግዴታ የለባቸውም:: ነገር ግን እነኝህ ጥቂቶች ከኛ ልዩ የሚያደርጋቸው ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነታቸውን አጥብቀው ይወዳሉ፤ እንዲጠቃባቸውም አይፈልጉም:: ኢትዮጵያ የርሃብ አገር ወይንም የመጨረሻዋ ድሃ አገር ተባለች ለነሱ ኢትዮጵያ ታላቅና ታሪካዊ አገር ናት:: የረሃብም የድህነትም አገር ያደረጓት ብቃትና ራዕይ የሌላቸው አምባገነኖች የመንግሥት ወንበሩን ስለያዙት ነው:: ቅንጅት አኮ ረሃብን ከኢትዮጵያ ውስጥ በአምስት ዓመት ውስጥ አጠፋለሁ ብሎ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቃል ገብቷል:: ኢትዮጵያ የተፈጥሮና የሰው ኃይል ጸጋ ያላት አገር ናት:: አሁን የተያዘው ትግል ይህን ኃይል በሥራ ላይ እንዳናውል ነው:: ይህ ኃይል በሥራ ላይ እንዲውል ከፈለግን አንዱንና ብቸኛውን ቅንጅትን እንደግፍ:: የምንችለውን የገንዘብ፣ የሀሳብ፣ የዲፕሎማሲ አስተዋጽኦ እናድርግ:: ድል አኮ ከፊታችን ሆኖ በርቱ እንጂ ይላል:: HR-2003 በአሜሪካ ሴኔት እንዲጸድቅ የምንችለውን ሁሉ እናድርግ:: ድሉን የማቃረብ ሚና አለው::

ሌላ ሁላችንም በምንችለው ዘዴና መንገድ ለአቶ መለስ ዜናዊ የምናስተላልፈው ልዩ መልዕክት አለ:: ይህም መልዕክት እንዲህ የሚል ነው፤

> በግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም የሕዝብ ምርጫ ታላቅ ታሪካዊ ሥራ ተሰርቷል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ የመንግሥት ሥልጣን ምንጩ እርሱ ብቻ መሆኑን አምኖ ተገንዝቦ ብዙ ድካምና እንግልት ደርሶበት ሳይበገር የኔ ነው የሚለውን ቅንጅትን መርጧል:: ቅንጅት ሥልጣን እንዳይረከብ ግድያ፣ አፈና፣ እስራት፣ ስደት ተፈጸመ:: እስካሁን በጠመንጃ ኃይል ሕዝብ የነፈገዎን ሥልጣን ይዘው አገር ያጠፋሉ፣ ሕዝብ ያንገላታሉ፣ ያስርባሉ፣ ያሰቃያሉ:: ምንም አሉ ምን ሀቁ ይህ ነው:: እንዳውም ይባስ ብለው ቅንጅት ያቀረበውን የምዝገባ ማመልከቻ የእርስዎ የምርጫ ቦርድ አልቀበልም ብሎ ይኸው እስካሁን አልተመዘገበም:: በመሆኑም ቢሮ ከፍቶ አርማውን ሰቅሎ እንደልቡ መንቀሳቀስ አልቻለም::
>
> አቶ መለስ ዜናዊ ከእንግዲህ በኢትዮጵያችን የፓለቲካ ጨዋታ ከግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም በፊት እንደነበርው እንደማይሆን ይረዱ:: የፖለቲካ መሬት መንቀጥቀጥ በዛች ዕለት ሆኗል:: ፓራዳይም ሺፍት (paradigm shift) ተፈጽሟል:: ሰዓቱን ወደ ኋላ መመለስ አይቻልም:: ስለሆነም አቶ መለስ ዜናዊ እንዲገነዘቡት የምንፈልገው ጸሎት አለ:: ጸሎቱም እንዲህ ይላል፤
> ***" Lord give me the courage to change the things which can and ought to be changed, the serenity to accept the things which cannot be changed, and the wisdom to know the difference. "***

እባክዎ ለራስዎም፣ ለቡድንዎም ሲሉ የተፈጸመውን ለውጥ ይቀበሉ፡፡ ቅንጅት የለም ብለው አይንዎን መጨፈን ብልህነት አይደለም፡፡ ቅንጅትን ከውስጥ ሆነው እንዲከፋፍሉት ብሎም እንዲያጠፉት የላኳቸው ሰዎች ተነቅቶባቸዋል፡፡ ተልዕኳቸው ግቡን አይመታም፡፡ ምክንያቱም ቅንጅት የኢትዮጵያ ሕዝብ አርማና ተስፋ ነውና፡፡ የሚያዋጣው መንገድ ቅንጅትን ሕጋዊ እውቅና ሰጥቶ በነኛ ስምንት ነጥቦች ላይ ከክቡር አቶ ኃይሉ ሻውልና አመራር ጋር መደራደር ነው፡፡ ይህን ማድረግ ደግሞ ላለፉት ሶስት ዓመታት ውስጥ በአገሪቱ ያንሳሳፈፈውን አስፈሪ የፖለቲካ ዳመና ያነሳዋል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዚህ አቋም ምንም ፍንክች እንደማይል ግልጽ ይሁንልዎ፡፡

በአጠቃላይ የኢትዮጵያን ሕዝብ የዲሞክራሲ ትግል የሚያዳክሙንና የሚከፋፍሉን በአሳፋሪ ስራቸው እናውግዛቸው፤

ውሸተኞችንና አሉባልተኞችን እንደማንቀበላቸውና የጥፋት ሥራቸውንም እንደምንቃወም ግልጽ እናድርግላቸው፡፡ በዚህ ይሉኝታ ሊኖር አይገባም፡፡ እነሱ ይሉኝታ ቢሶች ናቸውና፤

የቅንጅት ትግል የኛም ትግል ነውና ለከቡር አቶ ኃይሉ አመራር የምንችለውን የገንዘብ፣ የሃሳብ፣ የሞራልና የዲፕሎማሲ አስተዋጽኦ ሳንሰለች ድል እስከሚገኝ እናድርግ፤

HR2003 በአሜሪካ ሴኔት እንዲጸድቅ የምንችለውን ሁሉ እናድርግ፤

የክቡር አቶ ኃይሉ ሻውል አመራር ከእንግዲህ ወዲህ ለወያኔና ለውጭ ኃይል ምንደኞችና መልዕክተኞች ውሸትና አሉባልታ መልስ ለመስጠት ጠቃሚ ጊዜውን በፍጹም ማጥፋት የለበትም፡፡ የነሱ ፍላጎት ግን ይህ ነው፡፡ እውነተኛ ሥራ እንዲሰራ አይፈለጉም፡፡ ሥራ ከተሰራ ደግሞ የቅንጅት ትግል ወደፊት ይሄዳል፡፡ የኢትዮጵያም ሕዝብ ተስፋና ስሜት እንደገና ይቀጣጠላል፡፡

ለወያኔም፣ ለውጭ ኃይሎችና ለተላላኪዎቻቸው አንድ ጥሩ አድርገው ሊረዱትና ሊያውቁት የሚገባ ሀቅ አለ፡ እሱም ቅንጀት አንድ ነው፤ ቅንጀት እንደ ቅርጫ ስጋ አይከፋፈለም፤ ቅንጅትም የሚመራው በክቡር አቶ ኃይሉ ሻውል ፕሬዚዳንትነት ብቻ ነው፡፡

ቅንጀት አንድ ነው !
ኢትዮጵያም አንድ ናት!
የኢትዮጵያ ሕዝብ የቅንጅትን አርማ አንግቦ ያሸንፋል!

ወርቁ ሀብተማርያም
ቶሮንቶ